# ለምን ይዋሻል?

*ተመስገን ጌጡ*

‹‹የአብዮተኛው ትውልድ የተሸፋፈነ ኪሳራ›› በሚል ርዕስ፤ በያዝነው ወር በዚሁ ጋዜጣ የቀረበው ፅሑፍ መላ ቢስ ነው፡፡ ፀሐፊው ‹‹የአብዮተኛውን ትውልድ›› የሚተቹ መሆኑ አልደነቀኝም፡፡ እኔን የደነቀኝ፤ ወይም በጣም ግራ ያጋባኝ፤ ይኽ ሽፍንፍን የሚጠላው ፀሐፊ፤ በዓይን የሚታየውን፤ በእጅ የሚዳሰሰውን፤ ፍጥጥ ያለ ነገር ለመሸፋፈን መሞከሩ ነው፡፡ ፍላጎታቸው፤ በስም አዳሪ ዘይቤ ‹‹አብዮተኛ ትውልድ›› በሚል የሚጠቅሱትን ኢህአዴግ አሳንሶ ማሳየት በመሆኑ፤ የአኃዝ ቁጢት ሲበጥሱ ይታያሉ፡፡ ‹‹የተሸፋፈነ ኪሳራ›› ያንቀራብጣጣሉ፡፡

ፀሐፊው፤ ‹‹አብዮተኛው ትውልድ›› በሚል የሚጠቅሰው፤ ማለትም የአፄ ኃይለ ስላሴን መንግስት በአድሃሪነት የከሰሰው፣ ያፈረሰው፣ አፄአዊው ስርዓቱን ገልብጦ ሌላ መንግስት ያቋቋመው ትውልድ፤ የረባ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት መፍጠር እንዳልቻለ ይነግሩናል፡፡ ሐገሪቱን የኋላት አስጉዟታል ይሉናል፡፡ የዛሬው ትችት፤ እንደለመድነው አይዲዮሎጂን የተንተራሰ ትችት አይደለም፡፡ እንዲያውም የሚጠቅሱት የልማታዊ መንግስት አብነት ተደርጋ የምትታየውን ደቡብ ኮሪያን በአርአያ የሚያነሱ ናቸው፡፡

‹‹የአብዮተኛው ትውልድ›› የሚለውን ቃል በትዕምርተ ጥቅስ ውስጥ አስቀምጠውታል፡፡ ይህ የሚያመለክተው ምን እንደሆነ አላውቅም፡፡ ሆኖም ፀሐፊው ‹‹አብዮተኛው ትውልድ›› የሚሉት፤ ከአፄው ስርዓት ውድቀት በኋላ ስልጣን የያዙትን ሁለት መንግስታት መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ስለዚህ ‹‹አብዮተኛ ትውልድ›› የሚለው ቃል የደርግ እና ኢህአዴግ መንግስታትን ይጠቅሳል፡፡ እኒህ ሁለቱ መንግስታት፤ ከአፄ ኃይለ ስላሴ መንግስት ጋር የሚተካከል የኢኮኖሚ ዕድገት መፍጠር አልቻሉም ይላሉ፡፡ እንዲያውም፤ ‹‹ያለፉት ሠላሳ ዓመታት የኋሊት የተጓዝንባቸው፤ በጣም የሚያስቆጩ የባከኑ ዓመታት ዓመታት ናቸው›› ይላሉ፡፡ 30 ዓመታት ከድህነት ወደ ብልፅግና ለመጓዝ የሚያስችል ዘመን እንደሆነ፤ ደቡብ ኮሪያን አብነት በማድረግ ያስረዳሉ፡፡

የፀሐፊው አቀራረብ የተሳከረ ነው፡፡ ትንታኔው ውል የሌለው ነው፡፡ ትኩረቱ ፈር ያጣ ነው፡፡ ፀሐፊው አስቀድመው የያዙትን መደምደሚያ እውነት ለማድረግ ሲሉ ይሉኝታ በሌለው ሁኔታ ያትታሉ፡፡ አያያዛቸው፣ ‹‹በሁለቱ መንግስታት ዘመን ምንም ዓይነት ዕድገት አልተመዘገበም›› ማለት እንደ ፈለጉ ያስታውቃል፡፡ እንዲያውም በግልፅ ‹‹ያለፉት ሠላሳ ዓመታት የኋሊት የተጓዝንባቸው ዓመታት ዓመታት ናቸው›› ይላሉ፡፡ ሆኖም በሐተታቸው ውስጥ የሚነበበው ክርክር፣ ሁለቱ ‹‹አብዮተኛ›› መንግስታት ከአፄው ዘመን የተሻለ ኢኮኖሚያዊ የዕድገት አላስመዘገቡም የሚል ሳይሆን፣ ዕድገት ቢያስመዘግቡም ምጣኔው ከአፄ ኃይለስላሴ ዘመን ጋር ሲነፃፀር ዝቅተኛ መሆኑን የሚገልፅ ነው፡፡ ፀሐፊው ‹‹ወደ ኋላ ሄደናል›› እያሉ፣ በሐቲታቸው የሚሞግቱት ‹‹በአብዮቱ ዘመን ፈጣን ዕድገት አልተመዘገበም›› በሚል ነው፡፡

የዕሑፉ አቀራረብ በጥናት የተደገፈ ነው፡፡ ግራፍ ተጠቅሟል፡፡ የሦስት ምሁራንን ጥናት ያጣቅሳል፡፡ የመቶኛ ስሌቶችን እያስቀመጠ ይከራከራል፡፡ ግን ትንታኔው ወግ ማረግ የሌለው ነው፡፡ ፅሑፉ በገፅታው ወይም በአቀራረቡ፣ የአዋቂ ሰው ፅሑፍ ይመስላል፡፡ ሆኖም በይዘቱ፣ ዕውቀት ያጠጠው ሰው ሥራ ይመስላል፡፡ በፅሑፉ አቀራረብ እና ይዘት የተፈጠረብኝ ስሜት በዘይቤ ቢገለፅ፣ የኮሌጅ ደጅ ያልረገጠ ሰው፣ የአንዱን ተመራቂ ‹‹ጋወን›› ለብሶ ፎቶግራፍ እንደተነሳ ዓይነት ነው፡፡ የሁለቱ ሰዎች ሁኔታ አንድነት፣ ‹‹ዋናው ነገር መምሰል እንጂ መሆን አይደለም›› በሚል እምነት የሚመሩ መሆናቸው ነው፡፡ የፅሑፉ አቅራቢ፣ እውነታውን ፎቶ ማንሳት ሳይሆን፣ የሚፈልገውን ነገር መሳል ነው፡፡ በፅሑፉ የምናየው ችግር የተፈጠረው ከዚህ የተበላሸ ፍላጎት ነው፡፡ ፀሐፊው የሚፈልጉትን ሐሳብ ለመሳል ሲሞክሩ፣ ሐተታው ይበልጥ አሳማኝ እንዲሆንላቸው ሳይንሳዊ የአቀራረብ ዘይቤ መከተልን መርጠዋል፡፡ ስለዚህ ምሁራንን ምስክር ይጠራሉ፡፡ የአባቱን ሱሪ የለበሰ ኩታራ አስመሰላቸው እንጂ አልቻሉበትም፡፡ የጀመሩት አካሄድ አልሆን ሲላቸው ይሸፍጣሉ፡፡ ይቆርጣሉ፡፡ ደግሞ ይቀጥላሉ፡፡

# ሦስቱ ምስክሮች

ፀሐፊው፣ በመንደርደሪያ የሚያነሳቸው ሦስት የጥናት ፅሁፎች አሉ፡፡ የጥናቶቹ የእርሳቸውን አቋም የሚደግፉ አይደሉም፡፡ ግን እንደዚያ ጋወን ለባሽ ብጤ፣ የክርክራቸውን ባዶነትን ለመሸፈን የተጠሩ በመሆናቸው፣ ለጊዜው ዓላማቸው ተሳክቷል፡፡

ፀሐፊው፤ የምሁራኑን ጥናት እንደ ጋወን ለብሰው ይፈርዳሉ፡፡ ሐሰት ይኮተኩታሉ፡፡ ከጥናታዊ ዕሑፎቹ የማይገኝ መደምደሚያ እያወጡ ክርክራቸውን ያደምቃሉ፡፡ አውዱ የማይፈቅደውን፤ አጥኝዎቹ የማይቀበሉትን ሐሳብ እና መደምደሚያ በድፍረት እየወሰዱ ይፅፋሉ፡፡ በነውር የሆነ ትርጉም ያወጣሉ፡፡ ቆርጠው ይቀጥላሉ፡፡ ‹‹አብዮተኛው ትውልድ›› የሚሉትን ለማሳጣት እንዲያገለግሉ ያስገድዷቸዋል፡፡

በሦስቱ ምሁራን የተሰሩትን ጥናቶች በመጥቀስ፤ ከአብዮቱ በፊት ‹‹በኢትዮጵያ የሥልጣኔ መንፈስ ተፈጥሮ ነበረ፣ በትምህርት ዘርፍ ትልቅ ስኬት ተመዝግቦ ነበረ፣ ለዕድገት ትልቅ ፋይዳ ያለው አዲስ ባህል ተፈጥሮ ነበረ›› የሚል ክርክር ያራምዳሉ፡፡ ሆኖም፤ የሦስቱ ጥናታዊ ፅሑፎች ድምዳሜ፤ ፀሐፊው ከሚሉት ጋር ግልፅ ቅራኔ ያለው ቢሆንም፤ ምሁራኑን አላግባብ ምስክር አድርገው ያቆሟቸዋል፡፡ በመጀመሪያ፤ ፀሐፊው ‹‹በዘመኑ ብቅ ብሎ የነበረው ሥልጣኔ ብሩህ ተስፋ ወኪል›› ሲሉ ያወደሷቸውን እና በ1950ዎቹ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ተማሪዎች የነበሩትን ተማሪዎች የተመለከተ ጥናት ያቀረቡትን ምሁር ሥራ እንመልከት፡፡

የዊልያም ሻክ ጥናት ትኩረት እና ዓላማ፤ የከተማ ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ለተለያዩ የሥራ መስኮች የሚሰጡትን የከበሬታ በደረጃ ማወቅ፣ በዚያ ላይ ተመስርቶ፤ በከተማ ህይወት ማቆጥቆጥ ጋር ተያይዞ የመጣውን የእሴት እና የማህበረሰብ አደረጃጀት ለውጥን መቃኘት፤ የለውጡን ባህርይ፣ ጥልቀት እና ፍጥነት መመዘን ነው፡፡

የዊልያም ሻክ ጥናት የሚዳስሰው የ1950ዎቹን ሁኔታ ነው፡፡ ይህ ወቅት በአፍሪካም ሆነ በኢትዮጵያ የከተሞች መስፋፋት የታየበት ወቅት ነው፡፡ አዲስ ክስተት የሆነው የከተሞች መስፋፋት፤ አዲስ ማህበራዊ አደረጃጀት መፍጠሩን የሚጠቅሱት ሻክ፤ በዘመናዊት ኢትዮጵያ የሚታየውን ይህን አዲስ ክስተት፤ በዘመናዊት አፍሪካ እያቆጠቆጡ ባሉ ከተሞች ውስጥ ካለው ሁኔታ ጋር ያነፃፅራሉ፡፡ በወቅቱ፤ መጠነኛ ስልጠና እና ትምህርት ለተቋደሱ አፍሪካውያን ደመወዝ ለማግኘት የሚያስችል አዳዲስ የሥራ ዕድል እየተፈጠረላቸው ከመምጣቱን የሚያነሱት ሻክ፤ በህብረተሰቡ ዘንድ ትልቅ ማህበራዊ ከበሬታ ወይም ማዕረግ ለማግኘት የቻሉ ማህበራዊ ቡድኖች እየተፈጠሩ እንደመጡ ይጠቅሳሉ፡፡

እንደ ሌሎች የአፍሪካ የከተማ ነዋሪዎች ሁሉ፣ የኢትዮጵያ የከተማ ነዋሪዎችም አዲስ ማህራበዊ ማዕረግ በሚያቀዳጁ የተለያዩ ሙያዎች ወይም የሥራ መስኮች ለመሰማራት የሚችሉበት ዕድል መፈጠሩን ጠቅሰው፣ በዚህ የተነሳ፣ ከተለያዩ የጉልበት ሥራዎች ጋር ተያይዞ የቆየው ነባር እሴት ወይም አመለካከት፣ ከአዲሱ ሁኔታ ጋር መጣጣም እና መለወጥ እንደጀመረ ይገልፃሉ፡፡ የኢትዮጵያ የከተማ ነዋሪ ህዝብ ማህበራዊ መስተጋብርም እየተለወጠ መምጣቱን ያስረዳሉ፡፡

በኢትዮጵያ እና በሌሎች አፍሪካ ሀገራት የከተማ ነዋሪዎች ዘንድ ለታዩት ለውጦች ዋነኛው ምንጭ፣ ህብረተሰቡ የኑሮ መሠረት ያደረጋቸው አዳዲስ የሥራ መስኮች ናቸው፡፡ በተፈጠረው በዚህ ለውጥ ሳቢያ፣ ሙያ እና ክህሎት ያላቸው ከተሜዎች ከፍ ያለ ማህበራዊ ሥፍራ እና ደመወዝ በሚያስገኝ አዳዲስ የሥራ መስኮች መሰማራት ቻሉ፡፡ የተፈጠሩት አዳዲስ የሥራ መስኮች በህብረተሰቡ ዘንድ ከሚያስገኙት ከበሬታ አንፃር ያላቸውን ደረጃ ለመረዳት የመሞከር ሁለት ፋይዳዎች እንደሚኖሩት የሚገልፁት አጥኚው፣ በአንድ በኩል፣ የከተማ ነዋሪ በሆነው ህብረተሰብ ዘንድ ያለው ተዋረዳዊ የአደረጃጀት ስርዓት (social stratification) ምን መልክ እንዳለው ለመረዳት ከማስቻል ባሻገር፣ በህብረተሰቡ ውስጥ የሚታየውን የለውጥ ሂደት ለመለካት መነሻ ሊደረግ የሚችል የመመዘኛ መስፈርትም ሊሰጠን እንደሚችል ሻክ ያስረዳሉ፡፡

በዘመናዊት ኢትዮጵያ የሚታየው የሙያ መስክ ስምሪት እና ምርጫ፣ በሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ከሚታየው ሁኔታ የተለየ እንዲሆን ያደረገ አንድ ወሳኝ ነጥብ መኖሩን የሚናገሩት ሻክ፣ ለምሣሌ፣ በማዕከላዊ አፍሪካ በሚገኙት ሁለት ሐገሮች - ዛየር እና ዛምቢያ- ከሥራ መስኮች ምርጫ እና ስምሪት አንፃር የሚታየውን ሁኔታ ለማጥናት የተደረጉ ጥናቶች የሚያመለክቱት፣ ሐገራቱ በቅኝ ግዛት ተይዘው በነበሩበት ዘመን፣ ከፍተኛ ክህሎት የሚጠይቁ እና ፕሮፌሽናል የሚባሉ የሥራ ቦታዎች በሙሉ በአውሮፓውያኑ የተያዙ እና በእነዚህ መሰኮች አፍሪካውያን እንዳይሳተፉ በረቀቀ ዘዴ ሲገፉ መቆየታቸውን ነው ይላሉ፡፡

አያይዘው፣ በኢትዮጵያ እንዲህ ዓይነት ሁኔታ እንደማይታይ አመልክተው፣ በሌሎቹ የአፍሪካ ሀገራት፣ አውሮፓዊ ወይም አፍሪካዊ መሆን በሙያ ምርጫ እና ሥምሪት ረገድ ልዩነት ያመጣ እንደነበረ በመጠቆም፣ በኢትዮጵያ የከተማ ነዋሪ ህብረተሰብ ተዋረዳዊ

ማህበራዊ እርከን ውስጥ የተለያየ ደረጃ እና ማህበራዊ ምንጭ (ከተለያዩ ብሔር/ብሔረሰቦች) የተውጣጡ ተማሪዎች ለመሰማራት የሚችሉባቸውን ልዩ ልዩ የሙያ መስኮች ደረጃ እንዲሰጡ ተጠይቀው፣ ምላሻቸው ከሞላ ጎደል ተመሣሣይ ሆኖ እንደተገኘ አመልክተዋል:: እንግዲህ የአዲስ አድማሱ ፀሐፊ ‹‹ጉድ ጉድ›› እያሉ ያወሩት ይህንን ጉዳይ ነው፡፡

በመቀጠል፣ አዲስ አበባ በተመሠረተች በሁለት አስርት ዓመታት ውስጥ በከተማዋ ነዋሪ ህብረተሰብ ከሙያ መስክ ስምሪት እና ከብሔር አኳያ የሚታየው ተዋረዳዊ ማህበራዊ ድልድል ግልፅ መልክ መያዙን የጠቀሱት አፐኒው፣ በ1910 (እኤአ) ዓ.ም ቁጥሩ ወደ 65 ሺህ ገደማ ከነበረው የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ ህዝብ ውስጥ የፖለቲካ እና የባህል የበላይነቱን የጨበጠው እና ማህበራዊ ማዕረግን የሚወስነው ቡድን ድርሻ ከጠቅላላው ከ10 በመቶ ያነሰ እንደነበረና የሙያ ደረጃ ተዋረዱም የሚወስነው በዚሁ ቡድን እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ ዝቅተኛ ተደርጎ የሚታየው ሙያ እና ማህበራዊ ደረጃም፣ የበላይነቱን ከያዘው ማህበራዊ ቡድን የራቀ ባህል እና ማህበራዊ ሰልፍ ጋር የተያያዘው ነው፡፡

በ1900ዎቹ፣ ከአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች በቁጥር አነስተኛ የሆኑት ከፍተኛ የሚባለውን ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ማዕረግ የያዙ ሲሆኑ፣ የሚበዙት ዝቅተኛ በሚባለው ማህበራዊ እርከን እንዲሰለፉ የተደረጉት የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ናቸው፡፡ እነዚህም፣ በችርቻሮ፣ በጅምላ ንግድ፣ በዕደ ጥበብ፣ በቀን ሠራተኛ እና በቤት ሠራተኛ የሥራ መስኮች የተሰማሩ መሆናቸውን ሻክ አመልክተዋል፡፡ ስለዚህ፣ ማህበራዊ አደረጃጀቱ ሙያ እና ብሔር የተሳሰሩበት ነበር፡፡

አዲስ አበባ በተቋቋመች በመጀመሪያዎቹ ዓመታት ተጓዥ ሆነው ወደ ከተማይቱ የመጡና በዚህቺው ከተማ ለብዙ ጊዜ የኖሩ አንድ ሰው በወቅቱ ስለነበረው ሁኔታ ያሰፈሩትን ቃል ዊልያም ሻክ ይጠቅሳሉ፡፡ ‹‹በሰሜኑ አውራጃ በሚኖረው ህብረተሰብ ዘንድ ለጉልበት ሥራ ዝቅተኛ አመለካከት ይሰጣል፡፡ እናም በዚያው በሚኖሩበት ሀገራቸው ዝቅተኛ አድርገው የሚያዩትን ያንኑ የጉልበት ሥራ ከመስራት ባይገላገሉም፣ የያዙት አመለካከት የጉልበት ሥራ ፍለጋ ወደ መዲናዋ በሰፊው እንዳይሰደዱ አድርጓቸዋል፡፡ ስለዚህ፣ በአብዛኛው በአዲስ አበባ የጉልበት ሥራ የሚሰሩት ከማዕከላዊው እና ከደቡቡ የሀገሪቱ አውራጃዎች የመጡ ጉራጌዎች እና ኦሮሞዎች፣ እንዲሁም ውሱን ቁጥር ያላቸው ፈላሻዎች ናቸው፡፡

በድሮው ጊዜ፣ ፈላሻዎቹ በሰሜኑ ኢትዮጵያ ነዋሪዎች የሚነወሩ ሥራዎችን ለመስራት ፈቃደኛነት ያላቸው መሆኑ ይታያል›› ማለታቸውን የጠቀሱት ዊልያም ሻክ፣ ‹‹ከኢትዮ-ጣሊያን ጦርነት በኋላ የሀገሪቱ የኢኮኖሚ መሠረት እየሰፋ የተለያዩ የሥራ መስኮች ብቅ ብቅ ያሉበት ሁኔታ ቢፈጠርም፣ ብዙዎች ኢትዮጵያውን እና ምዕራባዊ ታዛቢዎች ከሰሜን የኢትዮጵያ አውራጃዎች የወጡ ከተሜዎች ለሥራ ያላቸው ግምት አሁንም በነባሩ እሴት ላይ የተተከለ እንደሆነ ያስባሉ›› ካሉ በኋላ፣ ሆኖም የእርሳቸው የጥናት ውጤት ይህን ግምት የማይደግፍ መሆኑን አመልክተዋል፡፡

ዊሊያም ሻክ፣ ይህ ግምት በሀገሪቱ የተጀመረው ምዕራባዊ ትምህርት እና ሥልጠና በህበረተሰቡ አስተሳሰብ ላይ የፈጠረውን ሰፊ ለውጥ የሚያድበሰብስ እና እየተለወጠ እና እየዘመነ ባለ ህብረተሰብ ባህላዊ አውድ ውስጥ ሰሜነኞቹ ኢትዮጵያውያን ነባር እሴቶቻቸውን በምን እኳኋን እየከለሷቸው እንደሆነ እንዳናይ የሚያደርግ ነው ሲሉ ዕፈዋል፡፡

የታዲያ የአዲስ አድማሱ ጸሐፊ ይህችን ይዘው፣ የ1950ዎቹ ተማሪዎች ‹‹ይሂኛው ሙያና ይሂኛው የኑሮ ዘይቤ ለአማራ፣ ለኦሮሞ ወይም ለሶማሌ ተወላጅ ነው፡፡ ያኛው ሙያና ይሂኛው የኑሮ ዘይቤ ደግሞ ለትግራይ፣ ለወላይታ ወይም ለጉራጌ ነው፣ የሚሉ የዘልማድ አዝማሚያዎችን አይቀበሉም›› ቢሉም፣ በጥናቱ ውስጥ በግልጽ የሰፈሩ ይህን ድምዳሜ የሚቃረኑ ጉዳዮች አሉ፡፡

ተማሪዎቹ ከተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች የመጡ ቢሆንም፣ በሙያ ምርጫቸው እንደሚመሳሰሉ የጠቀሱት የሚሉት የአዲስ አድማሱ ፀሐፊ፣ አያይዘው ‹‹በያኔው የስልጣኔ ጭላንጭል፣ ለዕውቀትና ለሳይንስ፣ ለሙያና ለምርታማ ሥራ ክብር የሚሰጥ ትውልድ እየተፈጠረ ነበር፡፡ ይህም በአገሪቱ እየታየ የነበረውን የትምህርትና የኢኮኖሚ አቅጣጫ ያመለክታል›› ይሉናል፡፡ ‹‹አሁን እንዲህ ነገር የለም›› ወይም ‹‹ከዛ ወዲህ ባሉት ዓመታት ይህ መልካም ዝንባሌ እየተዳከመ ነበር›› ማለታቸው እንደሆነ ግልፅ አይደለም፡፡ ግልፅ ያደረጉት ነገር፣ ‹‹የያኔው የስልጣኔ ጭላንጭል ተዳፍኖ ለ30 ዓመታት የ ኋልዮሽ ስንጓዝ ቆይተናል›› የሚለውን አመለካከታቸውን ነው፡፡

ዊልያም ሻክ እንደ ጠቀሱት፣ ልዩ ሥልጠና ለሚጠይቁ እንደ ዶክተር፣ ኢንጂነር፣ መምህር ላሉ የሙያ ዘርፎች፣ አክብሮት የሚያሳዩት ተማሪዎች ብቻ ሳይሆኑ፣ የገጠርም ሆነ የከተማ

ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ለተጠቀሱት የሙያ ዘርፎች ከፍተኛ ግምት ይሰጡ እንደነበረ አመልክተዋል፡፡ ስለሆነም ተማሪዎቹ፤ ለህክምና፣ ለኢንጂነሪንግ እንዲሁም ለአስተማሪነት ሙያ ከፍተኛ ግምት መስጠታቸው በተለየ የሚታይ አይደለም፡፡

በጥናቱ፤ ሙያዊ የሚባሉት የሥራ ዘርፎች (ዶክተር፣ ኢንጂነር፣ አስተማሪ፣ ዳኛ፣ ሜዲካል አሲስታንት) ዝቅተኛ ነጥብ (9.16) እንዲይዙ ያደረገ አንድ ጉዳይ መኖሩን የተቀሱት ዊልያም ሻክ፤ ሙያ በሚል ምድብ  የተካተቱት የስራ መስኮች አጠቃላይ ውጤት ዝቅ እንዲል ያደረገው፤ ተማሪዎቹ ‹‹ዳኛ›› እና ‹‹ሜዲካል አሲስታንስ›› በሚል ለተጠቀሱት የሙያ ዘርፎች ዝቅተኛ ነጥብ በመስጠታቸው እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ የዳኝነት ሙያ ዝቅተኛ ግምት ወይም ነጥብ (11.79) ያገኘውም፤ ነባሩ ልማዳዊ ህግ ከአውሮፓውያን የህግ ስርዓት ጋር እንዲመሳሰል ለማድረግ የተጀመረው ሂደት በህብረተሰብ ዘንድ ሰፊ ጥርጣሬ በመፍጠሩ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ተማሪዎቹ በመካኒክ እና በኢንጂነሪግ ሙያ መካከል ያለውን ልዩነቱ በግልፅ እንደማይረዱት በማውሳት፤ በተለይ ሰሜነኞቹ ለመካኒክ ሙያ ዝቅተኛ ግምት እንዳላቸው አረጋግጠዋል፡፡ ኢትዮጵያውያኑም እንደ ሌሎች ሀገራት ዜጎች ሁሉ ለመሬት ባለቤትነት ትልቅ ግምት የሚሰጡ ቢሆንም፤ ሆኖም የተማሩት ወጣቶች በግብር የመሰማራት እና ገጠር የመሄድ ፍላጎት የላቸውም ብለዋል፡፡

በተማሪዎቹ የደረጃ ምደባ ውስጥ የደመወዝ ጉዳይ ብዙ ትኩረት ያልተሰጠው ነገር መሆኑንም የጠቆመው ጥናቱ፤ በመንግስት መስሪያ ቤቶች የደረጃ ዕድገት ለማግኘት ዝምድና ወይም የት/ቤት ጓደኝነት ወሳኝ የሆኑበት መንግስታዊ መዋቅር መኖሩንም አረጋግጧል፡፡

የአማራ እና የትግራይ ተወላጅ የሆኑት ተማሪዎች፤ በማህበረሰባቸው ዘንድ ከፍተኛ ግምት የሚሰጣቸውን የሥራ ዘርፎች፤ ማለትም የቤተክርስቲያን ሰባኪነትን እና ግብርናን በመተው፤ የእጅ ሙያ ወይም አናጢን ለመሳሰሉ ሥራዎች የተሻለ ነጥብ መስጠታቸው፤ ነባሩ አስተሳሰብ እየተቀየረ መሆኑን ጠቋሚ እንደሆነ የጠቀሱት ሻክ፤ ዝቅተኛ ተደርገው የሚታዩ አንዳንድ ሥራዎች የተወሰኑ ብሔረሰቦች ልዩ ሀብት ተደርገው የሚታዩበት ሁኔታ መኖሩንም ጠቁመዋል፡፡ አክለውም፤ በማህበራዊ አውዱ ዳርቻ ያሉ ላይ የሚገኙ ብሔር/ብሔረሰቦች ተወላጆች ለወታደርነት ከፍተኛ ግምት እንደሚሰጡ ጠቅሰው፤ ይህም

የሆነው ውትድርና ወደ ከፍተኛው ማህበራዊ እርከን በቀላሉ ለመውጣት የሚያችል በር አድርገው ስለሚያዩት መሆኑን አመልክተዋል፡፡

ከዚህ ሌላ፤ ከ1960-1970 ዓ.ም (እ.ኤ.አ) በመላ ኢትዮጵያ የህዝብ ትምህርት መስፋፋት፤ ከሀገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት ምጣኔ በእጅጉ የላቀ በመሆኑ፤ ከት/ቤት የወጡ ተማሪዎች ሰፊ የሥራ ዕድገት የሚፈልጉበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ በጠቅላላ የሀገሪቱ አውራጃዎች ምንም ዓይነት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት እንደ ሌለ፤ የሀብታምና የመሳፍንት ቤተሰብ ያልሆኑ ወንዶች ተማሪዎች በገጠር እና በከተማ በሚገኙ ጥቂት የአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች ውስጥ ለመማር የነበራቸው ዕድል እጅግ ጠባብ እና እንደ ተአምር በሚቆጠር አጋጣሚ የሚገኝ ዕድል መሆኑን የሚያስረዳ ጥናት ነው፡፡

‹‹አማራ›› የሚለው ቃል በጥናታቸው ሜተዶሎጂያዊ ችግር እንደፈጠረባቸው የሚጠቅሱት ሻክ፤ የከተሜው ህዝብ ግንኙነት በብሔረሰብ ማንነት ላይ የተመሰረተ እንዳልሆነ ጠቁመው፤ በኢትዮጵያ የሚታየው የማህበራዊ ህይወት ለውጥ ሂደት Westernization ከሚባል ይልቅ ‹‹Amharization›› ሊባል የሚገባው መሆኑን መስክረዋል፡፡ በብዙዎቹ የአፍሪካ ሀገራት ውስጥ ‹‹የምዕራብ ስልጣኔን›› መያዝ ወይም ‹‹የአውሮጳውያን የኑሮ ዘይቤ›› መከተል የከፍተኛ ማህበራዊ ማዕረግ መገለጫ ሆኖ እንደሚታይ ጠቅሰው፤ በኢትዮጵያውያን ዘንድ የሚታው ሁኔታ ከሌሎች አፍሪካዊ ከተሜዎች የተለየ አስተሳሰብ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ በእነዚህ ሐገራት የልሂቅ ወግ ወይም ባህል አብነት (cultural models) የአውሮጳውያን እንጂ የአፍሪካውያን ከተሜዎች የኑሮ ወግ አልነበረም፡፡

ሆኖም፤ በአዲስ አበባ እና በሌሎቹ የኢትዮጵያ ክፍላተ- ሀገራት ከተሞች በሚኖሩት የከተማ ነዋሪዎች ዘንድ፤ የልሂቅ ወግ ወይም የባህል አብነት ሆኖ የፀናው የፖለቲካ የበላይነት የያዘው ቡድን ምግባር እና እሴት ላይ ነው፡፡ የከፍተኛ ማዕረግ ውስጥ በሆነው ቡድን በአማራ ነው፡፡ ስለሆነ፤ በኢትዮጵያ የሚታየው ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ለውጥ ሂደት ሊገለጥ የሚችለው በአማራዊነት እንጂ በምዕራባዊነት አይደለም፡፡ ከዘመናዊ ትምህርት፣ ከቴክኖሎጂ፣ ከቋንቋ ከቁሳዊ ሸቀጦች ወዘተ ጋር የተያያዙት አውሮፓዊ ወይም ምዕራባዊ እሴቶችና ወጎች (Norms)፤ የኢኮኖሚው ማህበራዊ ህይወት መዋቅር መሰረት ከሆነው የአማራ የኑሮ፣ የእሴት የልማድ ማዕቀፍ ውስጥ ገብቶ እንደገና ይተረጎማል፡፡ በመሆኑም፤

በኢትዮጵያውያኑ ዘንድ የተለየ ከበሬታ ያገኘ ምዕራባዊ ባህል ካለ፤ ያ ምዕራባዊ ባህል የበላይነት በያዘው ቡድን ዘንድ ከበሬታ ያገኘ ስለሆነ ነው ይላሉ፡፡

የትምህርት ስርጭቱን አስመክተው ያሉት ነገር አለ፡፡ በተለያዩ አውራጃዎች የነበረው የትምህርት ስርጭት፤ ዜሮ ለመባል የቀረበ እንደነበረና፤ የትምህርት ዕድሉ ለተወሰኑ ወገኖችን ያደላ እንደነበረ አስረድተዋል፡፡ የትምህርት ዕድሉ የሀብት እና የማህበራዊ ምንጭ የበላይነት ካለው ማህበራዊ ቡድን የወጡ ልጆች ተጠቃሚ የሆኑበት፤ የድሀ ልጆች ባሉት የ1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመማር ዕድል የሚያገኙት በልዩ ዕድል መሆኑን ገለፀዋል፡፡ በቤተሰብ ማህበራዊ አቋም፣ በሀብት፣ በትውልድ የትምህርት ዕድል የሚያገኝበት (በመንግስቱም- በግሉም) ዘመን እንደነበረም ጠቅሰዋል፡፡

እንግዲህ አብዮቱን የወለደው ይህ ማህበራዊ ማህፀን ነው፡፡ ፀሐፊው የጠቀሷቸውን ጥናቶች በትክክል ለማንበብ እና ለመረዳት ቢሞክሩ ኖሮ፤ በምሁራኑ በተፃፉት ጥናቶች ውስጥ የአብዮቱን ሽል መመልከት በቻሉ ነበር፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ፤ አብዮቱን ያፈነዱት ራሳቸው አፄ ኃይለስላሴ እንጂ ተማሪዎቹ አይደሉም፡፡ የአብዮቱን ተቀጣጣይ ንጥረ ነገር ሲያከማቹ የነበሩት የስርዓቱ ባለቤቶች ናቸው፡፡ የአብዮቱ ተቀጣጣይ ንጥረ ነገር በረጅም ጊዜ ሂደት እየተጠራቀመ መጥቶ ነበር፡፡ በአፄ ኃይለስላሴ ዘመን ትምህርት በከፍተኛ ፍጥነት መስፋፋቱን እንዲያስረዱላቸው  የጠቀሷቸው ዶ/ር ተከስተ ነጋሽ ባቀረቡትም ሆነ በሌሎቹ ምሁራን ጥናቶች ውስጥ የምናነበው ‹‹የብሩህ ተስፋ›› መዝሙር ሳይሆን የአብዮት እንጉርጉሮ ነበር፡፡ በጥናቱ ተሳታፊ ከሆኑት ተማሪዎች፤ ፤ ምናልባት ሁሉም ወይም የተወሰኑት፤ የአብዮተኛው ትውልድ አባላት መሆን ብቻ ሳይሆን መሪዎች ሳይሆኑ እንደማይቀሩ እገምታለሁ፡፡ ‹‹ማደግ ጀምሮ የነበረውን የስልጣኔ ፅንስ አስወረዱ›› በሚል የሚወቅሷቸው ተማሪዎች፤ ፀሐፊው እንዳሉት ብሩህ ተስፋ የሚታያቸው ወጣቶች ነበሩ፡፡ ሆኖም፤ እነዚህን ወጣቶች ወደ አብዮት የገፋቸው፤ የሰብዕና ጉድለት ወይም ልዩ የባህርይ እንከን ወይም ጀብደኝነት ሳይሆን በህዝቡ ላይ ይወርድ የነበረ ግፍ ነው፡፡

የዶ/ር ተከስተ ነጋሽ ጥናት የትምህርት ስርዓቱ የከሰረ መሆኑን የሚያስረዳ ነው፡፡  ዶ/ር ተከስተ ነጋሽ፤ በሦስቱ መንግስታት በተተገበሩት የትምህርት ፖሊሲዎች ውስጥ ያዩትን ችግር በሚያትቱበት ጥናታቸው፤ በአፄ ኃይለስላሴ ዘመን የመስፋፋቱ ሂደት ፍትሃዊ ያልሆነ እና አዝጋሚ እንደሆነ ዘልቆ፤ በኋላ የትምህርት ሥርዓቱ የሚያመርታቸውን

ተማሪዎች የሚቀበል የኢኮኖሚ ዕድገት ባለመፈጠሩ የተከተለውን ቀውስ ያሳሉ፡፡ የተበላሸ ፖሊሲ ውሎ አድሮ ሀገሪቱን ወደ ከፋ ችግር ሲከታት እንመለከታለን፡፡ በመጨረሻ፣ ‹‹ሴክተር ሪቪው›› የሚባል የትምህርት ስርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም ተነድፎ፣ ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት አብዮቱ መፈንዳቱን እንገነዘባለን፡፡ የዶ/ር ተከስተ ጥናት እንዲህ ያሉ ነገሮችን የሚያነሳ እና የሐዘን ወይም የቁጭት ስሜት የነገሰበት ጥናት ነው፡፡ እኔ እንደማስታውሰው፣ ዶ/ር ተከስተ ነጋሽ በጥናታቸው የተሻለ የትምህርት ፖሊሲ የሚሉት በዘመነ- ኢህአዴግ የተነደፈውን የትምህርት ፖሊሲ ነው- የሚጠቅሷቸው አንዳንድ ችግሮች እንዳሉ ሆኖ፡፡

የአዲስ አድማሱ ፀሐፊ የጠቀሱት ሌላው ጥናት የሜሲንግ ጥናት ነው፡፡ የሻክ ሜሲንግ ጥናት በአፄ ኃይለስላሴ ዘመን የነበረው ኢትዮጵያን የማዘመን ጥረት በብዙ ረገድ ፈተና የተጋረጠበት መሆኑን የሚያረዳ ነው፡፡ የሚሲንግ ጥናት እንደሚያመለክተው፣ ኢትዮጵያን የማዘመን እንቅስቃሴው ‹‹በግለሰብ ሞገስ›› (በአፄው አርአያነት) ላይ የተንጠላጠለ ሰንካላ ጉዞ እንደነበር የሚገልፅ ነው፡፡

በአጠቃላይ ሦስቱም ጥናቶች የስርዓቱን አደገኛ ጉድለቶች የሚያሳዩ እንጂ ጥንካሬውን እና የብሩህ ተስፋ ዘመን መፈጠሩን የሚገልፁ ባይሆንም፣ የአዲስ አድማሱ ፀሐፊ ‹‹በእጅጉ የሚያስቆጭ ዘመን፣ በንጉሱ ጊዜ ቀረ›› የሚለውን ትረካቸውን ለማሳመር ጥናቶቹን ይጠቅሳሉ፡፡ በመነሻዬ ‹‹የተውሶ ጋዎን›› ያሰየኘኝም ይኸው ችግር ነው፡፡ በአጠቃላይ፣ የአዲስ አድማሱ ፀሐፊ፣ ‹‹የአብዮተኛው ትውልድ ውድቀት›› እያሉ በሚያነሳሱት ወቀሳ ባልስማማም፣ በዚያ ትውልድ ውስጥ ሊጠቀሱ የሚችሉ ችግሮች መኖራቸውን እቀበላለሁ፡፡ ግን እንዳሳቸው ‹‹የንጉሱ ዘመን ቀረብኝ›› አልልም፡፡ በዚያ ትውልድ ውስጥ እንደ ችግር ሊጠቀሱ የሚችሉት ችግሮችም የተፈቱት፣ በትክክለኛ ግምገማ ችግሮቹን ለይቶ ትክክለኛ የትግል  አቅጣጫ በተከተሉት የዚያው የአብዮተኛው ትውልድ አባሎች ነው፡፡

አብዮቱን ለጅብ አሳልፈው የሰጡትን፣ በተሳሳተ የትግል አመራር የብዙ ወጣቶችን ህይወት በከንቱ ያስቀጠፉትን፣ ሀገሪቱ በደም አበላ እንድትታጠብ ምክንያት የሆኑትን፣ በፖለቲካ ሽኩቻ እና በአንጃ ታምሰው ትግሉን ለተስፋ መቁረጥ ዳርገውት የነበሩትን፣ የህዝቡን ተስፋ ሊያመክን ሌላ ፊት ለብሶ ለመጣ የአምባገነን አገዛዝ አሳልፈው የሰጡትን፣ ‹‹የአብዮተኛው ትውልድ›› አባላት መከራችንን ስላበዙት ወቃሻቸው ነኝ፡፡ ሆኖም፣ የአዲስ

አድማሱ ፀሐፊ ‹‹ቀረብን›› ያሉትን ዘውዳዊ ስርዓት በመቃወም ስለመነሳታቸው፤ ትክክለኛ የህዝብ ጥያቄዎችን በማንገብ አብዮቱን ስለመጥራታቸው ግን አድናቂያቸው ነኝ፡፡

ፀሐፊው፤ ‹‹የኋልዮሽ ጉዞ ውስጥ የገባንበት›› ካሉት 30 ዓመታት ጊዜ ውስጥ 17 ሰባቱ እንዳሉት የኋልዮሽ ጉዞ ዓመታት ነበሩ፡፡ ይህ መጥፎ የታሪክ ምዕራፍ የመጣው ትክክለኛ የትግል ስትራተጂ ባለመከተል እና ውስጠ - ድርጅት ዲሞክራሲ እንዲያብብ ካለማድረግ ነበር፡፡ ሀገሪቱን የጦርነት አውድማ ያደረገውን እና በጅምላ እርምጃ የብዙ ወጣቶችን ውድ ህይወት ያለ ፍርድ የቀጠፈውን፤ ህዝቡንም ለዘግናኝ ረሃብ፣ እጅግ ለከፋ ድህነት እና ጉስቁልና የዳረገውን፤ ሀገሪቱ የኋልዮሽ ጉዞ እንድንይዝ ያደረገውን ወታደራዊ አገዛዝ ለማስወደግ 17 ዓመታትን የጠየቀ የትጥቅ ትግል ተካሂዷል፡፡ ትግሉም በስኬት ተደምድሟል፡፡ በእልህ አስጨራሽ ትግል ደርግ ከስልጣን ተወግዷል፡፡ የኢትዮጵያ የልማት እና የዲሞክራሲ ጉዞ ታወጇል - በ1983 ዓ.ም፡፡

# ውል የለሽ ንፅፅር

ስለ ኢኮኖሚያዊ ዕድገቱ ሲያትት ‹‹ሦስት እጥፍ፣ አራት እጥፍ፣ አስር እጥፍ፣ አስራ ስምንት እጥፍ፣ ሃያ እጥፍ›› እያሉ የንፅፅር ስሌት ያቀርባሉ፡፡ ስሌታቸው ስህተት አለው፡፡ አልፎ አልፎ ስሌታቸው ትክክል ሲሆን፤ ለንፅፅሩ የትኛውን ዘመን base line ወይም መነሻ አድርገው እንደወሰዱ ግልፅ አይደለም፡፡ ንፅፅር የሚያደርጉት የተለያዩ ዓመታትን base line አድርገው ነው፡፡ እንደ መነሻቸው ሁሉ መዳረሻቸውንም ይቀያይራሉ፡፡ እንደ ሁኔታው 1938፣ 1948፣ 1955ን ወዘተ መነሻ ያደርጋሉ፡፡ እንደ ሁኔታው 1992፣ 2003 ወዘተ መድረሻ ያደርጋሉ፡፡ የሦስት መንግስታትን የኢኮኖሚ አፈፃፀም ሲያነፃፅሩ፤ የአንዱን መንግስት የአስር ዓመታት አፈፃፀም፤ ከሌላኛው የሃያ ዓመታት አፈፃፀም አኃዝ ጋር ሲያወዳድሩ ይታያሉ፡፡

ለንፅፅር የቀረቡት ሦስት መንግስታት ናቸው፡፡ የአፄ ኃይለ ስላሴ መንግስት፤ ለ50 ዓመታት ገደማ በስልጣን የቆየ ነው፡፡ በእነዚህ ዓመታት፤ በአፄ ምኒልክ የተጀመረውን የስልጣኔ ጉዞ አስቀጥለዋል፡፡ ከዚያ ደርግ ለ17 ዓመታት ገዝቷል፡፡ ኢህአዴግ ደግሞ ሀገሪቱን ለሃያ ሁለት ዓመታት አስተዳድሯል፡፡ አሁንም በስልጣን ላይ ይገኛል፡፡ ፀሐፊው የሚያወዳድሩት እነዚህን መንግስታት ነው፡፡ የማወዳደሪያ ሚዛን የተደረገው ደግሞ፤ የ20

ዓመታት የማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ልማት አፈፃፀም ነው፡፡ ይህ ውድድር ለ17 ዓመታት በስልጣን ለቆየው ደርግ የሚመጥን አይደለም፡፡ እንዲህ ዓይነት ንፅፅር ለማድረግ ስንነሳ፣ የንፅፅሩ መስፈርት ተገቢ መሆኑን ከማሳየት መነሳት አስፈላጊ ቢሆንም፣ ፀሐፊው ይህን አላደረጉም፡፡ ሃያ ዓመቱን ለምን እንደመረጡ አይነግሩንም፡፡ የሆነ ሆኖ ‹‹በሃያ ዓመታት ውስጥ….›› እያሉ የሚያደርጉት ንፅፅር፣ ከኃይለስላሴ ዘመን የመጨረሻዎቹን ሃያ ዓመታት፣ ከኢህአዴግ ደግሞ የመጀመሪያዎቹን ሃያ ዓመታት በመውሰድ የሚደረግ ንፅፅር ነው፡፡ እንዲህ ዓይነት ንፅፅር ሳይንሳዊ አይደለም፡፡ የአባቱን ሱሪ የለበሰ ኩታራ አስመሰላቸው ያልኩት ይህን ነው፡፡ ግን በአቀራረብ ሳይንሳዊ ቅርፅ ሰጥቷቸዋል፡፡ መምሰሉ አዋጭ መስሎ ስለታያቸው ነው፡፡ የአንዱን ተመራቂ ‹‹ጋወን›› ወስዶ ፎቶግራፍ የተነሳ ሰው፣ በአዋቂነት ለመኮፈስ የሞክርበትን አስቂኝ ትዕይንት ትታዘባላችሁ፡፡ በአጭሩ ‹‹ሳይንሳዊ ወንጀል›› ተሰርቷል፡፡

# አራቱ መለኪያዎች

ከሁሉ አስቀድሞ፣ ‹‹ለ30 ዓመታት የኋልዮሽ ሄድን›› ብለው የተነሱ ቢሆንም በእርሳቸው ትንታኔ ውስጥ የምንመለከተው አነሰም በዛ ከዘውዱ በኋላ በመጡት ሁለቱ መንግስታት ዘመን በጠቀሷቸው የኢኮኖሚ መስኮች ዕድገት መመዝገቡን ነው፡፡ ስለሆነም፣ ወደ ኋላ የሚያነሱት ክርክር፣ ‹‹የኃይለ ስላሴ ዘመን የዕድገት ምጣኔ ከፍተኛ ነው›› የሚል ይሆናል፡፡ ነገሩ በዚህ ቢያበቃ ጥሩ ነበር፡፡ በስሌቱ እና በአኃዙ ላይ ሊነሳ የሚችለው ችግር እንዳለ ሆኖ፣ በአምስት ዘርፍ መድበው ባደረጉት ንፅፅር፣ በንጉሡ ዘመን፣ በመጨረሻዎቹ ሃያ አመታት፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ከሰላሳ እጥፍ በላይ ጨመረ›› ያሉት ፅሐፊው፣ ወቀሳው እንዳይቀርባቸው ‹‹በመጀመሪያዎቹ የኢህአዴግ አስር አመታትም እንዲሁ፣ የእድገት ፍንጭ አልታየም›› ካሉ በኋላ፣ ‹‹ከዚያ በኋላ ነው በፍጥነት ማደግ የጀመረው። በኢህአዴግ ሃያኛ አመት ላይ፣ የቴክኒክና ሙያ ተማሪዎች ቁጥር፣ ከሰላሳ እጥፍ በላይ በማደግ ከ350ሺ በላይ ሆኗል›› ይሉናል። ደግሞ የስልክ መስመሮች አገልግሎትን ያነሱና ሲደመድሙ፣ ‹‹እንደ ንጉሡ ዘመን ከስድስት እጥፍ በላይ እድገት የታየው በኢህአዴግ ዘመን ነው›› በማለት ያጠቃልላሉ፡፡ የኤክስፖርት ገቢን ያነሱና ‹‹ከአራት እጥፍ በላይ በማደግ፣ ከ2 ቢሊዮን ዶላር በላይ ሆኗል - በንጉሡ ዘመን ከተመዘገበው እድገት ጋር ተቀራራቢ ነው›› ብለው ይዘጋሉ።

አያይዘው ‹‹የእህል ምርትን ደግሞ እንመልከት›› የሚሉት ፀሐፊ፤ ‹‹ከአብዮቱ በፊት በነበሩ 20 ዓመታት፣ ለአንድ ሰው በአማካይ በየአመቱ 175 ኪሎ ገደማ እህል ይመረት ነበር›› ካሉ በኋላ፤ አሁንም ወቀሳው እንዳይቀር ‹‹በመጀመሪያዎቹ የኢህአዴግ አስር አመታት፣ የአገሪቱ የእህል ምርት፣ ከደርግ ዘመንም የባሰ ነበር - በየአመቱ በአማካይ ለአንድ ሰው 125 ኪሎ እህል ነበር የሚመረተው›› ይሉና በማጠቃለያቸው፤ ‹‹በእርግጥ ያለፉትን ስምንት አመታት ብቻ ካየን፣ የአገሪቱ የእህል ምርት እየተሻሻለ፣ በአማካይ 175 ኪሎ ገደማ እንደደረሰ እናያለን›› ይላሉ።

የአዲስ አድማሱ ፀሐፊ፤ ‹‹ከአፄ ኃይለስላሴ የተሻለ የኢኮኖሚ ዕድገት አላስመዘገበም›› በሚል የሚወቅሱትን የ‹‹አብዮተኛ ትውልድ›› የኢኮኖሚ ዕድገት አፈፃፃም ከንጉሱ ጋር ሲያነፃጽሩ፤ እንድ ጊዜ ብቻ የህዝብ ቁጥርን እንደ መከራከሪያ ነጥብ አንስተዋል፡፡ የንጉሱን የኢኮኖሚ ዕድገት አፈፃፀም ትልቅ ለማስመሰል የሚያግዝ ሲመስላቸው አሱት፡፡ እንዲህ እያሉ፤ ‹‹የአለም ባንክ መረጃ እንደሚያሳየው፣ በአብዮቱ ዋዜማ አመታዊው የኤሌክትሪክ ሃይል አቅርቦት 590 ጊጋዋትአወር ደርሶ ነበር። ግን በእነዚሁ አመታት ውስጥ የሕዝብ ቁጥርም ስለጨመረ፣ የኤሌክትሪክ ሃይል የማግኘት እድል በ18 እጥፍ ሳይሆን በ11 እጥፍ ነው የጨመረው።››

የኢኮኖሚ ዕድገቱን ገፅታ በትክክል ለማሳየት ወይም ለመዳኘት ከታሰበ፤ የህዝብ ቁጥር ጉዳይ በኤሌትሪክ ኃይል አቅርቦት ብቻ ሳይሆን በሁሉም ዘርፎች ታሳቢ መደረግ የሚገባው ነው፡፡ በአሁን ሰዓት ያለው የኢትዮጵያ ህዝብ ቁጥር ከንጉሱ ዘመን ጋር ሲነፃፀር በ50 ሚሊየን ይበልጣል -በንጉሱ ዘመን የህዝቡ ቁጥር 42 ሚሊየን ገደማ ልብ ይሏል፡፡ ከደርግ ከነበረው ጋር ሲነፃፀር ደግሞ በ30 ሚሊየን ይልቃል፡፡ ፀሐፊው ለንፅፅር የተከተሉት ዘዴ ውል የሌለው እና ብዙ የስሌት ችግር እንዳለበት አንዱ አመልካች ይህ ነው፡፡

በንጉሱ ዘመን የነበረው 42 ሚሊየን የህዝብ ቁጥር፤ በኢህአዴግ ዘመን ወደ 92 ሚሊየን አድጓል፡፡ ከአንድ እጥፍ በላይ ጨምረዋል፡፡ ይህ ጭማሪ እንደሳቸው ስሌት፤ ቀላል ዕድገት ነው፡፡ አንድ እጥፍ ጭማሪ ነዋ! ግን ከአንድ እጥፍ በላይ ሊባል የሚችለው ዕድገት የ50 ሚሊየን ሰዎች ጭማሪ ነው፡፡ በመሆኑንም፤ በኃይለ ስላሴ ዘመን የነበረው የእህል ምርት 175 ኪሎ በኢህአዴግ ከነበረው 175 ኪሎ ጋር እኩል ነው ሲሉ፤ የእህሉ ምርት

**(175 ኪሎ X በ50 ሚሊየን) ያህል ብልጫ እንዳለው ሳይጠቅሱ ነው፡፡ በኤሌትሪክ ኃይል የቤተሰብ ድርሻን በተመለከተ ያለው ሁኔታ ተመሳሳይ ነው፡፡**

ያም ሆኖ ፀሐፊው፣ ‹‹ኢትዮጵና ኢትዮጵያዊያን … ለ30 አመታት ያህል የኋሊት ተጉዘዋል›› ማለታቸውን አልተውም፡፡ ይህ የኋሊት ጉዞው ለ30 ዓመታት ማለትም ከ1966 እስከ 1996 ድረስ የዘለቀ ነው፡፡ የአዲስ አድማሱ ፀሐፊ ‹‹የንጉሡንና የአብዮቱን ዘመናት፣ የዛሬውንም ጭምር ለመመዘንና ለማነፃፀር የምንችልባቸው መረጃዎች ብዙ ናቸው። ዛሬ ጥቂቶቹን ብቻ እንመልከት›› በማለት ይነሳሉ።

**ንፅፅር የሚያደርጉባቸው አርዕስቶች ‹‹ትምህርት ከጀማሪ እስከ ዩኒቨርስቲ››፣ ‹‹ትምህርት በወንዶችና በሴቶች››፣ ‹‹የመሰረተ ልማት አቅርቦት››፣ ‹‹የእህል ምርትና እጦት›› የሚሉ ናቸው፡፡ ሆኖም፣ እነዚህን አርዕስቶች ለምን እንደመረጡ አያስረዱም፡፡** በአፄ ኃይለ ስላሴን ዘመን ትምህርትን ለማስፋፋት የተደረገውን ጥረት ሲያብራሩ ከ1938 ተነስተው እስከ 1966 ዓ.ም የሚዘልቁ መረጃዎችን ያነሳሉ፡፡ መረጃው የሃያ ስምንት ዓመታት ጉዞን የሚሸፍን ነው፡፡ የእርሳቸው ትኩረት የሃያ ዓመታት የዕድገት ምጣኔ ማነፃፀር ስለሆነ፣ የኢህአዴግን ዘመን ከ1983 እስከ 2003 ዓ.ም ድረስ ያለውን አፈፃፀም በማንሳት ተወስነዋል፡፡ በዚያው ስሌት የአፄውን 1946 እስከ 1966 ዓ.ም (ከ1947 እስከ 1967) ያለው ዘመን ይታያል ማለት ነው፡፡ ሆኖም እርሳቸው፣ ከዚያ በፊት ያለውን ከሃያ ዓመት የዘለለ አኃዝ ሲጠቅሱ ይታይል፡፡ የአዲስ አድማሱ ፀሐፊ እንዲህ ይላሉ፣

**‹‹በ1938 ዓ.ም የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ቁጥር፣ 35ሺ እንደነበር የሚገልፁት ዶ/ር ተከስተ ነጋሽ፣ ከአስር አመት በኋላ 95ሺ እንደ ደረሰ ይገልፃሉ - ዘጠና ሺ ገደማ የአንደኛ ደረጃ፣ አራት ሺ ገደማ የሁለተኛ ደረጃ፣ አራት መቶ ገደማ የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች። በ1955 ዓ.ም፣ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች አስር ሺ፣ የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ደግሞ 305 ሺ መድረሱን ዶ/ር ዶ/ር ተከስተ ነጋሽ ጠቅሰዋል … እንደገና ከአስር አመት በኋላ በአብዮቱ ዋዜማ፣ የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ቁጥር 1.04 ሚሊዮን ደርሷል - በሃያ አመታት ውስጥ ከአስር እጥፍ በላይ በማደግ።››**

ከጥቅሱ እንደሚታየው የ1938፣ የ1948 (በደፈናው ከአስር ዓመት በኋላ ብለው ያለፉት)፣ የ1955 እንዲሁም 1965 ዓ.ም አኃዞችን ጠቅሰዋል፡፡ የሃያ ለዓመታት አፈፃፀም ንፅፅር

መነሻ መሆን የሚገባውን (1946 ወይም 1947ን) ትተው፣ ከ1948 ተንተልጥለዋል፡፡ ምክንያቱም፣ ‹‹በሃያ እጥፍ ጨመረ›› ለሚል ቃል አጋኖ አልመች ስላላቸው ነው፡፡ ለንፅፅሩ የማያስፈልጉ ዘመናትን የተለያዩ ዘመናት አኃዞችን የጠቀሱት ደግሞ፣ አንባቢው ‹‹በሃያ እጥፍ ጨመረ›› ሲሉ የትኛውን ዘመን መነሻ አድርገው እንዳሰሉ በቀላሉ እንዳለይ ለማደናገር ነው፡፡ ሆኖም፣ 1938ን ጠቅሰው ‹‹ከአስር ዓመት በኋላ›› እንዳሉ ሁሉ መጨረሻውንም እቅጩን ሳይናገሩ ‹‹እንደገና ከአስር አመት በኋላ በአብዮቱ ዋዜማ›› ብለው ያልፉታል፡፡

የሆነ ሆኖ፣ በንጉሥ ኃይለስላሴ ዘመን፣ በ1948 ዓም፣ በሦስቱ የትምህርት እርከኖች (በአንደኛ፣ በሁለተኛ እና በከፍተኛ) ይማሩ የነበሩት ተማሪዎች አጠቃላይ ቁጥር 95ሺህ ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ 90ሺህ ገደማው የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች፣ 4000 ገደማው የሁለተኛ ደረጃ፣ 400 መቶ ገደማው የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች መሆናቸውን፣ የአዲስ አድማሱ ፀሐፊ ጠቅሰዋል፡፡

በ1948 ዓ.ም ተነስቶ እስከ ‹‹በአብዮቱ ዋዜማ›› ድረስ ባሉት ሃያ ዓመታት፣ 90ሺህ ገደማ የነበረው የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ቁጥር ወደ 1.04 ሚሊዮን ከፍ ማለቱን፣ ይህም ከአስር እጥፍ በላይ የሆነ ዕድገት መሆኑን፣ በሌላ በኩል በተጠቀሰው ሃያ ዓመታት ውስጥ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ቁጥር ከ4000 ገደማ ተነስቶ 190ሺ መድረሱን፣ በዚህም ከሃያ እጥፍ በላይ የሆነ ዕድገት መታዩትን፣ እንዲሁም የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች ቁጥር፣ ከአራት መቶ ገደማ ተነስቶ ወደ 6500 አካባቢ መጨመሩን፣ ይህም የአስራ አምስት እጥፍ ዕድገት መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ቁጥር በሃያ ዓመታት ውስጥ ከ90ሺህ ገደማ ወደ 1.04 ሚሊዮን ከፍ በማለቱ ከአስር እጥፍ በላይ (90 000 X 10 = 1.04 ማለት ነው) የሆነ ዕድገት መመዝገቡን፣ እንዲሁም በ1948 ዓ.ም 4ሺ ገደማ የነበረው የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ቁጥር፣ በ1966 ዓ.ም 190ሺ ገደማ በመድረሱ፣ በሃያ ዓመታት ውስጥ የአስራ አምስት እጥፍ (4000 X 20 = 190000 ማለት ነው) ዕድገት ማሳዩቱን፣ እንዲሁም 400 መቶ ገደማው የነበረው የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች ቁጥር፣ በሃያ ዓመታት ውስጥ ወደ 6500 በማደጉ፣ አስራ አምስት እጥፍ (400 X 15 = 6500 ማለት ነው) የሆነ ዕድገት መታዩትን አትተዋል።

በደርግ ዘመን በጠቅላላ በሦስቱ የትምህርት እርከኖች ከ3.8 ሚሊየን በላይ ተማሪዎች እንደነበሩ ይጠቅሳሉ፡፡ ከዚህ ውስጥ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት የተመዘገቡት ተማሪዎች ቁጥር ወደ 2.9 ሚሊዮን ገደማ መሆኑን ጠቅሰው፤ በ1966 ዓ.ም 190ሺ ገደማ የነበረው የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ቁጥር በደርግ ዘመን ወደ 900ሺ እንደተጠጋ ይገልፃሉ። ዕድገቱም የአራት እጥፍ ዕድገት መሆኑን ይጠቁማሉ ‹‹ከንጉሡ ዘመን ያነሰ ነው›› በማለት። የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች ቁጥር ደግሞ 18ሺ መድረሱን እና ይህም ወደ ሦስት እጥፍ ገደማ የሆ ዕድገት መሆኑን ያሰረዳሉ፡፡ በኢህአዴግ ጊዜ ደግሞ የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ቁጥር ከ2.9 ሚሊዮን ገደማ ተነስቶ፤ በሃያ ዓመታት ወደ 4.5 ሚሊዮን መድረሱን አመልክተው፤ ይህም የአምስት እጥፍ ገደማ ዕድገት እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡
በኢህአዴግ የሃያ ዓመታት የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች ቁጥር ከ18ሺ ተነስቶ ከ350ሺ በላይ መድረሱን እና ይህም ፣ እንደ ንጉሡ ዘመን የአስራ አምስት እጥፍ ዕደገት ነው ይላሉ፡፡
እኩል የአስራ አምስት እጥፍ ዕድገት አለ ማለት አሳሳች ነው፡፡ በንጉሡ ሃያ ዓመታት የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች ቁጥር ከ400 ተነስቶ በ1966 ዓ.ም 6500 ሲደርስ፤ በየዓመቱ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ይገቡ ነበሩት ተማሪዎች ቁጥር በአማካይ 325 ነበር ማለት ነው፡፡ በአንፃሩ በኢህአዴግ ዘመን፤ በየዓመቱ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ይገቡ ነበሩት ተማሪዎች ቁጥርበአማካይ 17 ሺህ 500 መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት የ17 ሺህ 175 ነው፡፡

በደርግ ዘመን መጨረሻ፤ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት የተመዘገቡት ተማሪዎች ቁጥር ወደ 2.9 ሚሊዮን ገደማ እንደነበረ የሚጠቅሱት የአዲስ አድማሱ ፀሐፊ፤ በንጉሥ ኃይለስላሴ ዘመን በነበሩ ሃያ ዓመታት ውስጥ የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ቁጥር በአስራ አምስት እጥፍ እንዳደገ ከገለፁ በኋላ ‹‹በኢህአዴግ 20 አመታት ውስጥስ?›› ሲሉ ይጠይቃሉ፡፡ በደርግ ዘመን መጨረሻ ከነበረው የ2.9 ሚሊዮን ገደማ የአንደኛ ደረጃ የተማሪዎች ቁጥር ወደ 15 ሚሊዮን ሲያድግ፤ በደርግ ዘመን ከነበረው ቁጥር ጋር ሲነፃፀር በአምስት እጥፍ ይበልጣል ይላሉ፡፡ ከዚያም ‹‹ተመልከቱ፤ በንጉሡ ሃያ ዓመታት ከአስር እጥፍ በላይ የጨመረው የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ቁጥር፤ በኢህአዴግ ሃያ ዓመታት የጨመረው በአምስት እጥፍ ብቻ ነው›› ይላሉ፡፡ በንጉሥ ኃይለስላሴ ዘመን የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ቁጥር በየዓመቱ

በአማካይ በ9ሽህ 500 ያድግ ነበር፡፡ በኢህአዴግ ሃያ ዓመታት ደግሞ የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ቁጥር በየዓመቱ በአማካይ በ750 ሺህ ይጨምር ነበር ማለት ነው፡፡ ልዩነቱም፤ 740 ሽህ ነው፡፡

ለመሆኑ፤ አንድ ማሰብ እና ማመዛዘን የሚችል ሰው ዘውዳዊው አፄ የኃይለስላሴ ዘመን መኖርን ይመርጣል ወይስ ችግሮች ቢኖሩም፤ ችግሩን በሰላማዊ መንገድ ለማረም በሚያስችለው፣ አነሰም በዛ ሐሳብን በነፃነት ለመግለፅ፣ በነፃ ለመደራጀት፣ የፖለቲካ ፓርቲ ለመመስረት ወዘተ በሚቻልበት ፌደራላዊ፣ ዲሞክራሲያዊ እና ሪፐብሊካዊ በሆነች ኢትዮጵያ መኖርን ይመርጣል፡፡ ጥያቄው ይኸ ነው፡፡

ማጠቃለል የምፈልገው ስለኢኮሚያዊ ዕድገት አንድ ነገር በማለት ነው፡፡ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ማለት በየዓመቱ በጥቂት በጥቂቱ የሚጠራቀም ዕድገት የሚመዘገብበት ሂደት ነው፡፡ በዚህም፤ በአንድ እና በሁለት ትውልዶች ዕድሜ ከፍተኛ የኑሮ ደረጃ ለውጥ የሚመጣበት ሂደት ነው፡፡ ዋናው ጉዳይ ዕድገቱ ቀጣይነት ያለው እንዲሆን የማድረጉ ጉዳይ ነው፡፡ ይህን ለማድረግ የሚስችሉ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ፖሊሲዎች የመኖራቸው ጉዳይ ነው፡፡ ሰላም እና መረጋጋትን ማስፈን የሚያስችል የፖለቲካ ስርዓት የመፍጠር ጉዳይ ነው፡፡ ዕድገቱ ሳይቋረጥ መዝለቅ ከቻለ ሊፈጠር የሚችልውን ሁኔታ በአንድ ምሣሌ ማየት ይቻላል፡፡

የኢትዮጵያውን የነፍስ ወከፍ ገቢ፤ 100 ዶላር ነው እንበል፡፡ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ለ10 ዓመታት በአንድ ፐርሰንት ቢያድግ፤ በ10 ዓመት የነፍስ ወከፍ ገቢ 110 ይሆናል፡፡ በ25 አምስት ዓመታት 128 ይሆናል፡፡ በ40 ዓመታት 149 ይሆናል፡፡ በ3 ፐርሰንት ቢድግ ደግሞ፤ በ10 ዓመታት የነፍስ ወከፍ ገቢ 134 ይሆናል፡፡ በ25 አምስት ዓመታት 209 ይሆናል፡፡ በ40 ዓመታት 326 ይሆናል፡፡ በ5 ፐርሰንት ቢድግ ደግሞ፤ በ10 ዓመታት የነፍስ ወከፍ ገቢ163 ይሆናል፡፡ በ25 አምስት ዓመታት 339 ይሆናል፡፡ በ40 ዓመታት 704 ይሆናል፡፡ በ8 ፐርሰንት ቢድግ ደግሞ፤ በ10 ዓመታት የነፍስ ወከፍ ገቢ 216 ይሆናል፡፡ በ25 አምስት ዓመታት 685 ይሆናል፡፡ በ40 ዓመታት 2ሺህ 172 ይሆናል፡፡ ቀመሩ $100\ (1+g)^t = F$ ነው፡፡ ለአርባ ዓመታት የተጠቀሰውን ዓይነት ዕድገት ያስመዘገበ አገር የለም፡፡ ከድህነት ወደ ባለፀጋነት የሄዱት ሀገሮች ለዓመታት (አንዳንዴም አስትር) ቀውስ ውስጥ ቢገቡም ዕድገታቸውን ለረጅም ዓመታት ማስቀጠል ስለቻሉ ነው፡፡ የአዲስ

አድማሱ ፀሐፊ ያጣጣሉትን የእድገት ምጣኔ እንደ አሁኑ አስቀጥለን መጓዝ ከቻለን ተአምሩን በህይወት እያለን በዓይናችን እናየዋልን፡፡

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ባለፉት ዘጠኝ ዓመታት ‹‹በዓለም እጅግ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት›› ተብሎ ከተመዘገበው የጃፓን፣ የቻይና እና የደቡብ ኮሪያ የዕድገት ምጣኔ ከፍ ባለ ሁኔታ የሁለት አኃዝ ዕድገት እያስመዘገበ መጥቷል፡፡ ይህን ዓለም የሚያደንቀውን የዕድገት ዕድገት በዚሁ መልክ ለተወሰኑ ዓመታት ከቀጠለ የሚፈጠረውን ተአምር አብረን እናያለን፡፡